ማዕድ ማጋራት 1 !!!

ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ ማህበራዊ ኃላፊነት የመወጣት ተግባሩን እንደቀጠለ ሲሆን ከልደታ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በቀረበለት ጥያቄ መሰረት ለማዕድ ማጋራት ተግባር የሚውል እና በአስር ኪ.ግ የታሸገ ከአንድ መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ብር ላይ የሚያወጣ አሥራ አምስት ኩንታል የስንዴ ዱቄት ጿጉሜ 01 ቀን 2015 ዓ.ም በድርጅታችን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መሥፍን አባተ እና ሥራ አመራር አባላት አማካኝነት ለጽ/ቤቱ ተወካዮች አስረክቧል፡፡



ዜና ማዕድ ማጋራት 2 !!!

በተለያዩ ሥራ መደቦች በትጋትና በቅንነት ሲያገለግሉ ቆይተው በጡረታ የተገለሉትን የቀድሞ ሥራ ባልደረቦቹን ባለመርሳት የሚታወቀው ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ አሁንም ይህንኑ ተግባር አጠናክሮ በመቀጠል ጳጉሜ 4 ቀን 2015 ዓ.ም አንድ መቶ ለሚሆኑ የቀድሞ የሥራ ባልደረቦቻችን አዲሱን የ2016 ዓ.ም ምክንያት በማድረግ ለእያንዳንዳቸው ሃያ አምስት ኪ.ግ የጤፍ ዱቄት፤አስር ኪ.ግ የስንዴ ዱቄትና አምስት ሊትር ዘይት በማበርከት የማዕድ ማጋራትና የምሳ ግብዣ አከናውኗል፡፡





በዚህም ወቅት የድርጅታችን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መሥፍን አባተ የቀድሞ ሥራ ባልደረቦቻችን ለድርጅታቸው ዕድገትና ለሀገራቸው ኢኮኖሚ ባለቸው ዕውቀትና አቅም ያደረጉት የጎላ አስተዋጽኦ ሊረሳ እንደማይቻል በመጠቅስ እንኳን ለ2016 ዓ.ም አዲስ ዘመን በሰላም በጤና አደረሳችሁ በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች የቀድም ሠራተኞችም በተደረገው ድጋፍ የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል፡፡

ጥራት መለያችን ነው!!

ብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ






SINCE
1906